መልእክት ስምንት

## እንደ እግዚአብሔር ቤት ለቤተ ክርስቲያን ጥበቃ
## የከተማይቱን ቅጥር መሥራት

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ነህ. 1፡3፤ 2፡9-20

**I. የዕዝራ መጽሐፍ የእስራኤላውያን ከምርኮ መመለስና የመቅደሱ መልሶ መገንባት ታሪክ ነው፤ የነህምያ መጽሐፍ የኢየሩሳሌም ከተማ ቅጥር መልሶ መሠራት ታሪክ ነው—ነህ. 2፡17-20፡-**

ሀ. የኢየሩሳሌም ከተማ በከተማው ውስጥ ለነበረው ለእግዚአብሔር ቤት ጥበቃና ከለላ ነበር—ቁ. 13፡-

1. ይህ የሚያመለክተው እንደ ማደሪያው እና በምድር ላይ እንዳለ ቤቱ፣ የእግዚአብሔር ቤት፣ እርሱ ኢኮኖሚውን ያከናውን ዘንድ ለአስተዳደሩ በምድር ላይ ያለውን የእርሱን ፍላጎት ለመጠበቅ መንግሥቱ እንደ ክልል መመሥረት እንደሚያስፈልገው ነው—ቁ. 15።
2. የእግዚአብሔር ቤት መልሶ መገንባት የዘቀጠችውን ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር መመለሱን በምሳሌ ያሳያል፣ የኢየሩሳሌም ከተማ ቅጥር መልሶ መሠራት እግዚአብሔር መንግሥቱን መመለሱን በምሳሌ ያሳያል—ቁ. 17-20።

ለ. እግዚአብሔር ቤቱን መገንባቱ እና መንግሥቱን መገንባቱ አብረው ይሄዳሉ—ማቴ. 16፡18-19።

**II. የነህምያ መጽሐፍ የመጀመሪያው ክፍል፣ ከምዕራፍ 1 እስከ 7፣ በነህምያ ክትትል የኢየሩሳሌም ከተማ ቅጥር መልሶ ስለመሠራቱ ነው፡-**

ሀ. ነህምያ የኢየሩሳሌም ቅጥር የመፍረሱንና በሮችዋም በእሳት የመቃጠላቸውን ዜና ሰማ—1፡3።

ለ. ነህምያ 2፡9-16 ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም ስላደረገው ጉዞና የኢየሩሳሌምን ከተማ ቅጥር ሁኔታ በተመለከተ ስለነበረው የግል ምልከታ ይናገራል።

ሐ. ነህምያ 2፡17-20 የኢየሩሳሌም ቅጥር መልሶ መሠራቱን የሚመለከት ቃል ነው፡-

1. መቅደሱ የጌታ መገኘት ስፍራ፣ ጌታን የምንገናኝበት እና የምናገለግልበት ስፍራ ነው፣ ሆኖም ጥበቃ ያስፈልገዋል።
2. የከተማይቱ ቅጥር ለመቅደሱ መከላከያ ነው፤ ያለ ከተማይቱ ቅጥር ጥበቃ የለም።
3. የከተማይቱ ቅጥር ለጥበቃ ብቻ ሳይሆን ለመለየትም ጭምር ነው።
4. የነህምያ መጽሐፍ ሁላችንም የቅጥሩን ድርሻችንን መሥራት እንዳለብን ይነግረናል፤ ሁሉም የየራሱን ድርሻ መሥራት አለበት—4፡6፣ 19።

መ. እንደ እግዚአብሔር ቤት፣ እንደ ማደሪያ ስፍራው ለቤተ ክርስቲያን ጥበቃ "ቅጥሩን የመሥራት"፣ ቤተ ክርስቲያንን እንደ የእግዚአብሔር መንግሥት የመገንባት፣ የነህምያን ምሳሌ ውስጠ-መሠረታዊ በሆነ መንገድ መከተል ያስፈልገናል—2፡4፣ 10፣ 17-20፤ ኤፌ. 2፡21-22።

**III. የቅጥሩ መሠራት ዓላማ በክርስቶስ ራስነት ሥር በሕይወት ወደሆነ ተገቢ ሥርዓት ውስጥ እኛን ለማምጣት ነው—1፡22-23፤ ቆላ. 1፡18፤ 2፡19፡-**

ሀ. ክርስቶስ፣ በጋራ የአካሉ፣ የቤተ ክርስቲያን ራስ፣ በግል የአማኞች ሁሉ ራስ ነው፤ እርሱ በቀጥታ የእያንዳንዳችን ራስ ነው—1፡18፤ 1 ቆሮ. 11፡3።

ለ. የቤተ ክርስቲያን ሕይወት በክርስቶስ ልዩና ብቸኛ ራስነት ሥር የመጠቅለል ሕይወት ነው—ኤፌ. 1፡10፣ 22-23፤ 4፡15-16፤ ቆላ. 2፡19።

ሐ. የክርስቶስን ልዩና ብቸኛ ራስነት ካከበርን፣ በጌታ ምለሳ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ቤቱ ብቻ ሳትሆን ከተማይቱም ጭምር ትሆናለች—ዕብ. 11፡10፤ ዕዝ. 1፡2-3፤ ነህ. 1፡9፤ 2፡5፣ 17፤ 1 ጢሞ. 3፡15፤ ራእ. 21፡2፣ 10-11፡-

1. ቤተ ክርስቲያን እንደ ቤቱ በዋናነት ሕይወት ከሆነው ክርስቶስ ጋር የተገናኘች ናት፣ ቤተ ክርስቲያን እንደ ከተማዋ በዋናነት ራስ ከሆነው ክርስቶስ ጋር የተገናኘች ናት—1 ጢሞ. 3፡15፤ ማቴ. 5፡14፤ ቆላ. 3፡4፤ 1፡18፡-
   - ሀ. ክርስቶስን እንደ ሕይወት ስንለማመድና ስንደሰት ቤተ ክርስቲያን እንደ ቤቱ አለችን፤ ልዩና ብቸኛ የሆነውን የክርስቶስን ራስነት ስንገነዘብ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደምታመለክተው ከተማ ትተልቃለች—ማቴ. 16፡18-19።
   - ለ. ቤተ ክርስቲያን እንደ ከተማዋ የምትገነባው በክርስቶስ እንደ ሕይወት ብቻ ሳይሆን በክርስቶስ ራስነትም ጭምር ነው፤ ስለዚህ፣ ክርስቶስ ሕይወታችን ብቻ ሳይሆን ራሳችንም ሊሆን ይገባል—ቆላ. 3፡4፤ 1፡18፤ 2፡19።

2. የክርስቶስን ልዩና ብቸኛ ራስነት ካከበርን፣ ለንጉሡ እና ለመንግሥቱ ቤተ ክርስቲያን ከቤት ወደ ከተማ ትተልቃለች—መዝ. 48፥1-2፤ 1 ቆሮ. 1፥2፤ 12፥12-13፣ 27፤ ኤፌ. 1፥22-23፤ 4፥15-16፤ ራእ. 21፥2፣ 10-11፣ 14፤ 11፥15።

## IV. ከሐዋርያት ትምህርት ተጻራሪ ከሆኑ ልዩ ትምህርቶች ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅ ቅጥሩን መገንባት ያስፈልገናል—ሐዋ. 2፥42፤ 1 ጢሞ. 1፥3-4፦

ሀ. ልዩ ትምህርቶች ከእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ጋር የማይጣጣሙ ትምህርቶችን ያመለክታሉ—6፥3።

ለ. በ 1፥3-4፣ 6-7፤ 6፥3-5፣ 20-21 ያሉት ልዩ ትምህርቶች እና በ4፥1-3 ውስጥ ያሉት ኑፋቄዎች የቤተ ክርስቲያን ውድቀት፣ ዝቅጠትና መበላሸት ዘሩ፣ ምንጩ ናቸው።

ሐ. ልዩ ትምህርት ማስተማር የእግዚአብሔርን ግንባታ ያፈርሳል፣ የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚም ያጠፋል፤ በልዩ መንገድ የሚሰጥ አነስተኛ መጠን ያለው ትምህርት እንኳን ሳይቀር ምለሳውን ያፈርሳል።

መ. ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና የእረኝነት እንክብካቤ፣ የሚያስፈልገው የመጀመሪያው ነገር ከእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ማዕከላዊ መስመር የቅዱሳንን ትኩረት አቅጣጫ የሚቀይር የተለየ ኃሳብ የሚያራምዱ ሰዎችን ልዩ ትምህርት ማስቆም ነው—ቲቶ 1፥9።

ሠ. ከልዩ ትምህርቶች መራቅ እና ስለ ክርስቶስ እና ስለ ቤተ ክርስቲያን በሆነው በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ላይ ማተኮር አለብን—1 ጢሞ. 1፥3-4፤ ኤፌ. 3፥9፤ 5፥32።

## V. ቅጥሩ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከተሠራ፣ የእግዚአብሔርን የግንባታ ሥራ ለማፍረስ ጠላት ከሚጠቀምባቸው ሰዎች እንጠበቃለን፦

ሀ. የመለኮታዊው ግንባታ አፍራሾች ኑፋቄዎችን የሚሰብኩትና የሚያስተምሩት ናቸው—2 ጴጥ. 2፥1፤ 2 ዮሐ. 7-11፦

1. የክርስቶስን ማንነት በተመለከተ ኑፋቄዎችን የሚያስተምሩ ሰዎች፣ ጌታ የሆነውን የጌታን ማንነት እና ጌታ አማኞችን የገዛበት ቤዛነቱን የሚክዱ የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ናቸው፤ ሰዉ ኢየሱስ አምላክ መሆኑን መካድ ታላቅ ኑፋቄ ነው—ቁ. 7፤ 1 ዮሐ. 2፥18፣ 22-23፤ 4፥2-3።
2. ሐዋርያው በኑፋቄዎቹ ተጽዕኖ ሥር እንዳይወድቁና የእውነትን ነገሮች እንዳያጡ ራሳቸውን ይጠብቁ ዘንድ አማኞችን አስጠንቅቋቸዋል፤ የክርስቶስን መፀነስና መለኮትነት የሚክዱትን ወደ ቤታችን ባለመቀበልና ሰላምታን ባለመስጠት መቃወም አለብን—2 ዮሐ. 8-11።

ለ. የመለኮታዊው ግንባታ አፍራሾች ከፋፋዮች፣ ቡድንተኞች ናቸው—ቲቶ 3፥10፦

1. ከፋፋይ ሰው መናፍቅ፣ በራሱ አመለካከቶች መሠረት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቡድኖችን በመፍጠር ክፍፍልን የሚያመጣ ቡድንተኛ ሰው ነው፤ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መልካም ሥርዓትን ጠብቆ ለማስቀጠል፣ ከፋፋይ ሰው ከመጀመሪያና ከሁለተኛ ተግሳጽ በኋላ ተቀባይነት ማጣት፣ መወገድ አለበት—ቁ. 10።
2. እንዲህ ያለው ከፋፋይነት ተላላፊ ስለሆነ፣ ይህ ተቀባይነትን ማሳጣት ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም ሲሆን ከከፋፋዩ ጋር ያለ ንክኪ ይቆም ዘንድ ነው—ተዛ. ዘኁ. 6፥6-7።

ሐ. የመለኮታዊው ግንባታ አፍራሾች የሚከፋፍሉ ሰዎች ናቸው—ሮሜ 16፥17፦

1. በሮሜ 14 ጳውሎስ በአስተምህሮ ወይም በተግባራዊ ልምምድ ልዩ የሆኑትን ሰዎች መቀበልን በተመለከተ ቦታ የሚሰጥ እና የሚፈቅድ ነው፤ ነገር ግን በሮሜ 16፥17 "እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን መለያየትንና ማሰናከያን የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ እለምናችኋለሁ፣ ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ" ሲል ጽኑ እና ቆራጥ ነበር።
2. ጌታ "በወንድማማች መካከል ጠብን የሚዘራን" ይጠላል—ምሳ. 6፥16፣ 19።

መ. የመለኮታዊው ግንባታ አፍራሾች ሥልጣን የማግኘት ምኞት ያላቸው ናቸው—3 ዮሐ. 9፦

1. በማንኛውም የጌታ ሥራ ውስጥ አንደኛ መሆንን ማሳደድ ፈጽሞ የለብንም፤ ይህ አንደኛ ለመሆን ከሌሎች ጋር ለመፎካከር ሳይታወቅ ውስጥ ውስጡን የሚሠራ ስውር የሆነ ምኞት የማሳካት ሥራ ነው—ቁ. 9።
2. የመለኮታዊው ግንባታ አፍራሾች ለመንጋው የማይራሩ ተኩላዎች እና አማኞችን ከኋላቸው ለማስከተል ጠማማን ነገር የሚናገሩ ናቸው—ሐዋ. 20፥29-30።

## VI. ቅጥሩ ከተሠራ በኋላ፣ በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚነጣጠር የሞትን ጥቃት መቋቋም እና በክርስቶስ የትንሣኤ ሕይወት የክርስቶስን አካል መገንባት እንችላለን—ማቴ. 16፥18፤ ዮሐ. 11፥25፤ ኤፌ. 1፥22-23፤ 4፥16፦

ሀ. ሞት የሰይጣን ሥራ ባሕሪ ነው፤ የሥራው የመጨረሻ ግብ ሰውን በሞት መሙላት ነው—ዕብ. 2፥15።

ለ. ማቴዎስ 16፡18 ቤተ ክርስቲያን ላይ የሚነጣጠር ጥቃት ከየትኛው ምንጭ እንደሚመጣ ያሳየናል—“ከገሃነም ደጆች” ያም ሞት ነው፡-

1. የሰይጣን ልዩ ዓላማ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሞትን ማሰራጨት ነው፣ ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ ታላቅ ፍርሃቱ የሞት ኃይሉን መቋቋሟ ነው—ራእ. 2፡8፣ 10-11።
2. “በዚህ ዓለት ላይ” የተገነባች ቤተ ክርስቲያን በሞትና በሕይወት መካከል መለየት ትችላለች፣ የገሃነም ደጆችም አይችሏትም—ማቴ. 16፡18።

ሐ. ክርስቶስን እንደ ፊተኛውና መጨረሻው—ሁሌም እንደሚኖረው፣ እንደማይለወጠው—እና ሞቶ እንደነበረው ሕያውም እንደሆነው—ትንሣኤ እንደሆነው ማንነት ማወቅ ያስፈልገናል—ራእ. 1፡17-18፤ 2፡8፤ ዮሐ. 11፡25፤ ሐዋ. 2፡ 24።

መ. የክርስቶስን አካል መገንባት የምንችለው በክርስቶስ የትንሣኤ ሕይወት ብቻ ነው—ኤፌ. 2፡6፣ 21-22፤ 4፡16፤ ራእ. 1፡ 18፤ 2፡8፤ ፊልጵ. 3፡10፡-

1. የክርስቶስ አካል በክርስቶስ የትንሣኤ ሕይወት ውስጥ ናት—ዮሐ. 11፡25፡-
   ሀ. ቤተ ክርስቲያን እንደ ክርስቶስ አካል ባሕሪዋ ትንሣኤ ነው—ሐዋ. 2፡24፤ ኤፌ. 1፡19-23።
   ለ. ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ትንሣኤ ውስጥና ከሞት በተነሣው ክርስቶስ የተፈጠረች አዲስ ፍጥረት ናት—1 ጴጥ. 1፡3፤ ኤፌ. 2፡6፤ ገላ. 6፡15።
2. የክርስቶስ አካል በትንሣኤ ናት፣ የትንሣኤ እውነታ ሕይወትን እንደሚሰጠው መንፈስ ክርስቶስ ነው—ዮሐ. 11፡ 25፤ 20፡22፤ 1 ቆሮ. 15፡45።
3. የትንሣኤ መርህ ተፈጥሮአዊው ሕይወት መገደሉና መለኮታዊው ሕይወት ስፍራውን ለመውሰድ መነሣቱ ነው—2 ቆሮ. 1፡9።
4. በተፈጥሮአዊው ሰው ሳይሆን በውስጣችን ባለው መለኮታዊ ሕይወት ስንኖር በትንሣኤ ነን፤ እንዲህ ያለው ኑሮ ውጤት የቤተ ክርስቲያን እንደ የክርስቶስ አካል ማደግና መገንባት ነው—ፊልጵ. 3፡10-11፤ ኤፌ. 4፡15-16፤ ቆላ. 2፡19፤ 3፡15።

*© 2022 Living Stream Ministry*